# የታሪፍ ማሻሻያ ኮሚቴ

## መመሪያ ቁጥር 228/2013

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

ሐምሌ 2006ዓ.ም

## መግቢያ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ቁጥር 153/2000 በተሰጠው ስልጣን መሰረት አምራቾች/ኢንዱስትሪዎች የታሪፍ ከለላ ጥያቄ ሲያቀርቡና ማግስት ልዩ ወሳኔ ሰሰጥ ታሪፍ የማሻሻል ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህም መሰረት የሚደረገው የታሪፍ ከለላ የሀገር ወስጥ ታዳጊ ኢንዱስትሪዎችን (Infant Industries) ተወዳዳሪነት ከማስደግና የውጭ ምንዛሪን ከማዳን አንፃር ያለወን ጠቀሜታ በአስተማማኝ ሁኔታ ለመመርመር እንዲሁም ማግስት በልዩ ወሳኔ የታሪፍ ማሻሻያ እንዲደረግ የሚሰጠው ውሣኔ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ለማመቻቸት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተወጣጣ የታሪፍ ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራወን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ይሁንና የታሪፍ ኮሚቴው ስራወን የሚያካሂደበት ወጥ የሆነ የአሠራር መመሪያ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ የታሪፍ ኮሚቴው አባላት ኃላፊነት፣ የኮሚቴወን የስልጣን ወሰን፣ የታሪፍ ከለላ ለማስጠት የሚያዩ ማስፈርቶች (ቅድመ ሁኔታዎች)፣ ወሳኔ የሚሰጥበት የጊዜ ወሰን እና ጥያቄ አቅራቢ አምራቾች/ኢንዱስትሪዎች ማሟላት ያለባቸወን ቅድመ ሁኔታዎች የሚዘረዝር የታሪፍ ኮሚቴው የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# የፌደራል ማግሥት የታሪፍ ከለላ ኮሚቴ
# መመሪያ ቁጥር 228/2013

## 1. አወጭው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚኒስትሮች ምክር ቤት የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ቁጥር 153/2000 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አወጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የፌደራል መንግስት የታሪፍ ከለላ ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 228/2013” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. “ታሪፍ” ማለት በገቢ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥና ታክስ ነው፡፡
2. “የታሪፍ ከለላ” ማለት የአገር ውስጥ አምራቾችን/ኢንዱስትሪዎችን ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ከሚፈጠር የንግድ ውድድር ተፅዕኖ መከላከል ነው፡፡
3. “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” እንደ ቅደም ተከተሉ ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ነው፡፡
4. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡
5. “አምራች” ማለት የታሪፍ ከለላ ጥያቄ የሚያቀርብ የአገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪ ነው፡፡

## 4. ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ የታሪፍ ከለላ አወሳሰን ወጥነት ያለው እና ግልጽ እንዲሆን ለማድረግ የታሪፍ ከለላ ኮሚቴን እና የባለድርሻ መ/ቤቶችን ኃላፊነት መወሰን ነው፡፡

## 5. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠውን የታሪፍ ከለላ፣ በልዩ ውሳኔ የሚሰጡ ማበረታቻዎችን፣ በታሪፍ መጽሐፉ ውስጥ የታሪፍ አመዳደብና መጣኔ ስህተት ለሚፈም የሚከናወኑ ተግባራትን እና በጉምሩክ ታሪፍ 2ኛ መደብ ሊስተናገዱ የሚገቡ ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 6. የታሪፍ ኮሚቴው አወቃቀር

1. ኮሚቴው ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተወከሉ ስምንት (8) አባላት ሲኖሩት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

2. የታሪፍ ማስተካከያ እንዲደረግለት ጥያቄ ያቀረበውን የሥራ መስክ የሚመራው የመንግስት መ/ቤት አንድ ተወካይ ጥያቄው በኮሚቴው በሚታይበት ጊዜ በአስረጂነት ሊጠራ ይችላል፡፡

## 7. <u>የታሪፍ ኮሚቴው ተግባራት</u>

የታሪፍ ኮሚቴው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ጥናት በማድረግ ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

1. በአምራቾች/በኢንዱስትሪዎች ወይም አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት የሚቀርቡ የታሪፍ ከለላ ጥያቄዎችን በመመርመር ወይም በራሱ አነሳሽነት ሊሰጥ ስለሚገባ የታሪፍ ከለላ፣

2. በአንደኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እንደ አስፈላጊነታቸው በሁለተኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፈልባቸው ወይም በሁለተኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈልባቸውን እቃዎች እንደአስፈላጊነታቸው በአንደኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ እንዲከፈልባቸው፣

3. በአንደኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ ላይ የሚያጋጥሙ የታሪፍ አመዳደብና መጣኔ ችግሮችን በመመርመር አመዳደቡ እንዲስተካከል፣

4. የታሪፍ ከለላው ሥራ ላይ የቆየበት ጊዜ ርዝመት የሥራ ዘርፉ ከውጭ ከሚመጡ ምርቶች ጋር ለመወዳደር ለሚያስፈልገው ዝግጅት በቂ ሆኖ ሲያገኘው ከለላው እንዲነሳ፣

5. በሚመለከታቸው መ/ቤቶች በኩል ማረጋገጫ እና ድጋፍ ሲቀርብ አገር ውስጥ በተፈላጊው ጥራትና መጠን ሊመረቱ የሚችሉ ምርቶችን በማየት የአንደኛ መደብ የጉምሩክ ቀረጥ ከፍ በማድረግ የታሪፍ ከለላ እንዲሰጥ፣

6. ከሚኒስትሩ በሚሰጥ ትዕዛዝ መሠረት በመንግስት ውሳኔ የሚሰጡ ማበረታቻዎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሁኔታ፣

## 8. <u>ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚከተለው አሠራር</u>

1. ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ ከሌሎች መካከል የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

ሀ) ግብአቱ ላይ የተጣለው የታሪፍ መጣኔና በሚፈሻ ምርቱ ላይ የተጣለው የታሪፍ መጣኔ ልዩነት፤

ለ) ከለላ እንዲሰጥባቸው የተጠየቁት ግብዓቶች ቀድሞ በሁለተኛ ሚዲብ እንዲስተናገዱ የተፈቀዱ ማሆን አለመሆናቸውን፤

ሐ) ምርቱ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት እና የውጭ ምንዛሬን የማዳን ጠቀሜታውን (Import Substitution and Foreign Currency Saving Role)፤

መ) የመንግስት የትኩረት አቅጣጫ

ሠ) በምርቱ ላይ ሀገሪቱ ያላት የአዋጪነት ደረጃ (comparative advantage & absolute advantage) ከፍተኛ ማሆን አለመሆኑን፤

ረ) ግብዓቱ ለሥራው ዘርፍ አስፈላጊ ማሆኑን፤

ሰ) የከለላውን አስፈላጊነትና ሊሰጥ የሚገባውን ከለላ ማጠን፣

ሸ) የሚደረገው ማስተካከያ ለኢንዱስትሪ ልማት (ኢንዱስትሪያላይዜሽን) ያለውን አስተዋፅኦ፣

ቀ) አግባብ ካለው የመንግስት አካል የሚቀርበውን የወሳኔ ሀሳብ፤

2. ተገቢውን የታሪፍ ወሳኔ ለማቅረብ እንዲረዳ የአምራቾችን የምርት ሂደት ማየት ሲያስፈልግ እና ተጨማሪ ሚጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኮሚቴው አባላት የማምረቻ ቦታዎችን ሊጎበኙ ይችላሉ፡፡

## 9. <u>የኮሚቴው አባላት ኃላፊነት</u>

የኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩባቸዋል፡፡

### 1. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተወካዮች</u>

ሀ) የታሪፍ ማስተካከያዎች የመንግስትን ገቢና ወጪ ግምት ወስጥ ባስገባ ሚልኩ የተደረጉ ማሆናቸውን ሚረጋገጥ፤

ለ) የሚተላለፈው የታሪፍ ማስተካከያ ወሳኔ በሕግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተሰጠው ሥልጣን ጋር የሚጣጣም ማሆኑን ሚረጋገጥ፡፡

### 2. <u>የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተወካዮች</u>

ሀ) አገሪቱ ከምትከተለው የኢኮኖሚ ኢንዱስትሪ ፖሊሲ አንፃር ጥያቄ ካቀረቡ ኢንዱስትሪዎች መካከል ለበረታቱ የሚባቸውን እና ከለላ የሚያስፈልጋቸውን ዘርፎች በጥናት ማለየት፤

ለ) የሚሟከታቸውን አካላት አስተያየት በማሰባሰብ የከለላው ማስጠት በሌሎች ኢንዱስትሪዎች ወይም በኅብረተሰቡ ላይ አሉታዊ ወጡትን የሚያስከትል መሆኑን ሚጋገጥ፤

ሐ) ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚፈለገወን ሚረጃ አደራጅቶ ማቅረብ፤

3. <u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተወካዮች</u>

የታሪፍ ከለላ እንዲደረግባቸው ጥያቄ የቀረበባቸውን ምርቶችና ግብአቶች የታሪፍ አመዳደባቸውን ትክክለኛነትን ሚጋገጥ እና እነዚህ ጥያቄዎች በጉምሩክ አፈፃፀም ላይ የሚያስከትሉት ችግር ካለ በማለየት ማጠቆም እና የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ፤

## 10. <u>የኮሚቴው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. የታሪፍ ከለላ እንዲሰጠው ጥያቄ የሚያቀርብ አምራች የሚጠበቅበትን ሙሉ ሚረጃ ሲያሟላ የኮሚቴው ፀሐፊ ለወይይት የሚሆን የመነሻ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለኮሚቴው አባላት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡ የኮሚቴ አባላቱም በተላከው መነሻ ሃሳብ ላይ ያላቸውን ግብአተ ሜልስ/አስተያየት በሦስት(3) ቀናት ወስጥ መሜለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2. ፀሐፊው በኮሚቴ አባላቱ የተሰጡ ተጨማሪ አስተያየቶችን እና ግብአተ ሜልስ አካቶ የወይይት ሀሳቡን ያዘጋጃል፡፡

3. ሰብሳቢው የኮሚቴ አባላቱን ስብሰባ በመጥራት በተዘጋጀው መነሻ ሃሳብ ላይ ወይይት እንዲደረግ እና የወሳኔ ሀሳብ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

4. ስብሰባወን ለማካሄድ የኮሚቴው አባል ከሆኑ መ/ቤቶች ቢያንስ አንድ ተወካይ እና 2/3ኛው መሟላት ይኖርበታል፡፡

5. በስብሰባው የሚቀርቡ የወሳኔ ሀሳቦች ተቀባይነት የሚኖራቸው በስብሰባው ላይ ከተገኙት መካከል ቢያንስ 51 በመቶ የኮሚቴው አባላት ሲስማሙበት ሲሆን፣ የኮሚቴው ድምጽ ካልተበላለጠ (እኩል በእኩል ከሆነ) ሰብሳቢው ድምፁ የሰጠበት ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

6. ሰብሳቢው የኮሚቴው አባላት የተስማሙበትን የወሳኔ ሃሳብ በማዘጋጀት አባላቱ እንዲፈራረሙ በማድረግ ለሜጨረሻ ወሳኔ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡

7. ሚኒስትሩ በሚሰጠው የሚጨረሻ ወሳኔ መሠረት ለባለሥልጣን መ/ቤቱ መመሪያ ይተላለፋል፡፡

8. በየጊዜው የሚቀርቡ የታሪፍ ክለሳ/ማሻሻያ ጥያቄዎች ተጠቃለው የማሻሻያ ውሣኔው ቢበዛ በአመት አራት ጊዜ (በየሩብ ዓመቱ) ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ይተላለፋል፡፡

## 11. የታሪፍ ማስተካከያ ወሳኔ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

1. የታሪፍ ማስተካከያ ወሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው የወሳኔወን ተፈፃሚነት የሚገልፀው መመሪያ ከተላለፈበት ቀን አንስቶ ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

2. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም የታሪፍ ማስተካከያው የታሪፍ ጭማሪን የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ማስተካከያው ከመደረጉ በፊት ሌተር ኦፍ ክሬዲት ተከፍቶ ወደአገር የሚገቡ ዕቃዎች ቀደም ሲል በሥራ ላይ በነበረው ታሪፍ መሠረት እንዲስተናገዱ ይደረጋል፡፡

## 12. የታሪፍ ማስተካከያ ጥያቄ አቀራረብ

የታሪፍ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ጥያቄ የሚያቀርቡ አምራቾች የሚከተሉትን ሚኒማዎች እና ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡-

ሀ) ዘርፉን ከሚመራው የመንግሥት መ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ፣

ለ) ከዚህ መመሪያ በተያያዘው ፎርም መሠረት ተገቢውን ማመልከቻና ፕሮፖዛል፣

ሐ) የግብአቶቻቸውንና የምርቶቻቸውን የጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር (HS CODE)፣

መ) የግብአቶቻቸውን ብዛትና ማጠን ስብጥር፣

ሠ) ግብዓቱ ለሚያመርቱት ምርት አስፈላጊ መሆኑን፣

ረ) ለማምረት የሚያወጡትን አጠቃላይ ወጪ አንድ ምርት ለማምረት የሚያወጡትን ወጪ ዝርዝር (Total Cost & Unit Cost) ማቅረብ፣

ሰ) ምርቶቻቸውን የሚያቀርቡበት ገበያ ሁኔታ (ሀገር ወስጥ ይሁን ለወጪ፣ ለሀገር ወስጥ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ ምርቱ ከወጪ የሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶችን ከመተካት አንፃር ያለበትን የተወዳዳሪነት ደረጃ እና የሽያጭ ዋጋ ማቅረብ፣

ሸ) የምርት ሂደቱ የሚያመጣው የቴክኖሎጂ ሽግግር (Technology Transfer) እና በአገር ወስጥ የሚጨመረው ተጨማሪ እሴት (Value Addition)

ቀ) ለወደፊት ሊያስገባ የሚችለውን የታክስ ገቢ ትንበያ (ግምት)፣

## 13. ሚጃ የማፃኘት መብት

የታሪፍ ማስተካከያ ጥያቄ አቅራቢዎች የሚከተሉት መብቶች ይኖራቸዋል፡-

ሀ) ጥያቄ ለማቅረብ ማሟላት የሚጠበቅባቸውን ሚጃዎች እና ቅድመ ሁኔታዎች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማግኘት፣

ለ) የግብአቶቻቸውንና የሚፈሻ ምርቶቻቸው የሚሟደበብትን የጉምሩክ ታሪፍ ቁጥር ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማግኘት፣

ሐ) የከለላ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያገኙ አመልካቾች ወሳኔ የተሰጠበትን ደብዳቤ ኮፒ (የሚሟከታቸው ገፅ ያለበትን ብቻ) ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## 14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዳስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ በሚኒስቴሩ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 15. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሐምሌ 15 ቀን 2006*

*ሱፍያን አህመድ*

*የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ*
*የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር*